የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፩፻፰
አዲስ አበባ መስከረም ፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 108
ADDIS ABABA 16th September, 2016

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፩/፪ሺ፰ ዓ.ም

የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ………………ገጽ ፱ሺ፫፻፲፪

CONTENTS

Proclamation No. 981/2016

Geothermal Resources Development Proclamation…………………………Page 9312

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፩/፪ሺ፰

## ስለጂኦተርማል ሀብት ልማት የወጣ አዋጅ

የጂኦተርማል ሀብት ተጠብቆና ለምቶ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም እንዲሁም ዕድገት መዋሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጂኦተርማል ሀብት ኤሌክትሪክ ኃይል ማመን ጨትን ጨምሮ ለአገሪቱ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ላላቸው አገልግሎቶች መዋሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚካሄዱ የጂኦተርማል ኃይል ማመንጨት ተግባራትን የሚደግፍ የሕግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ መኖር ለውጤታማ የጂኦተርማል ሀብት ልማትና ጥቅም ላይ መዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጂኦተርማል ሀብት ልማት እና ተግባራት ዓላማ ዎችን ከግብ ለማድረስ የሚመራ አዲስ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፪) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION No. 981/2016

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR GEOTHERMAL RESOURCES DEVELOPMENT

WHEREAS, it is necessary to ensure the conservation and development of geothermal resources for the social and economic benefit and growth of the country;

WHEREAS, it is necessary to ensure that the geothermal resources are utilized for the most economically benefits of the country, including electricity generation;

WHEREAS, putting in place the legal and regulatory framework to support geothermal power generation by the public and private sectors is essential to successful development and use of geothermal resources;

WHEREAS, it is essential to promulgate a new law which guides the achievement of the objectives of the geothermal resources development and operations;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (2) (a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፩/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የጂኦተርማል ሥራ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ተግባራት ናቸው፤

፪/ "የጂኦተርማል ሀብት" ማለት የማዕድንም ሆነ የውሃ ሀብት ወይም ቁሳዊ ንብረት ያልሆነ ነገር ግን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የጂኦተርማል ኢነርጂ፣ የጂኦተርማል ተረፈ ምርትን እና የጂኦተርማል ፈሳሽን የሚያካትት ተፈጥሯዊ የመሬት ሙቀት ነው፤

፫/ "የጂኦተርማል ኢነርጂ" ማለት በማንኛውም ሁኔታ ከመሬት ገፀ-ምድር በታች የሚገኝ ሆኖ ከተፈጥሮአዊ የመሬት ሙቀት የተገኘ ወይም የተፈጠረ ወይም ከዚሁ የተፈጥሮ ሙቀት ውስጥ የወጣ ኢነርጂ ነው፤

፬/ "የጂኦተርማል ተረፈ-ምርት" ማለት ዘይት፣ የሃይድሮ ካርቦን ጋዝና ሂሊየምን ሳይጨምር በመጠን፣ በጥራት ወይም በቴክኒክ ረገድ ለማውጣት ወይም ለማምረት አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት ራሳቸውን ችለው እንዳ ይወጡ ወይም እንዳይመረቱ በቂ ጠቀሜታ የሌላቸው ሆኖም ውህድ ሆኖ ወይም በጂኦ ተርማል እንፋሎት ውስጥ የሚገኙ ማንኛውም ማዕድን ነው፤

፭/ "የጂኦተርማል ፈሳሽ" ማለት ውሃ፣ ብራይንና እንፋሎትን አካቶ በሚገኝበት ከፍታ ወይም ጥልቀት ሙቀቱ ውሃ የሚፈላበት ደረጃ የደረሰም ይሁን ከዛ በላይ እንዲሁም ሙቀቱ የተገኘው በተፈጥሮም ይሁን በሪኢንጄክሽን ከጅኦተርማል ሀብት ጋር የተያያዘ ፈሳሽ ነው፤

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Geothermal Resources Development Proclamation No. 981/2016".

**2. Definitions**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "geothermal operations" means activities requiring a license to be issued pursuant to this Proclamation;

2/ "geothermal resources" means the natural heat of the earth, neither mineral resources, water resources or real property, but for the purposes of this Proclamation, includes geothermal energy, geothermal by-products, and geothermal fluids;

3/ "geothermal energy" means energy, in whatever form, exist below the surface of the earth, resulting from, or created by, or which may be extracted from such natural heat;

4/ "geothermal by-products" means any mineral exclusive of oil, hydrocarbon gas, and helium but which are found in solution or in association with geothermal steam and which, because of quantity, quality, or technical difficulties in extraction and production, are not of sufficient value to warrant extraction and production by themselves;

5/ "geothermal fluids" means those fluids associated with geothermal resources, including water, brines, and vapour, that have value by virtue of the heat contained therein, whether or not such fluids have a temperature that is the boiling point of water or greater than the boiling point of water at the altitude or depth of the occurrence, and whether the heat contained therein is naturally occurring or is transmitted in fluids artificially introduced into an underground formation;

፮/ "የጂኦተርማል ሀብት ክልል" ማለት ማንኛውም የጂኦተርማል ሀብት የተገኘበት ወይም የሀብቱ መገኛ እንደሆነ ታምኖ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሕዝብ ማስታወቂያ የተሰየመ ማንኛውም መሬት ነው፤

፯/ "የንግድ ማህበር" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

፰/ "ደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ብቃት ያለውና በዚያው አካባቢ እንደማሞቂያና የተቀናጀ ሙቀትና ኃይል የመሣሠሉ አገልግሎቶች መስጠት የሚችል ጂኦተርማል ሀብት ነው፤

፱/ "ደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትን ሣይጨምር የሙቀት ኃይሉን በቀጥታ ጥቅም ላይ ለሚያውሉ አገልግሎቶች፣ ለግብርና እና ለኢንዱስትሪ፣ ለመዝናኛ ገላ መታጠቢያ እንዲሁም ለህክምናና ለመሣሠሉ ሌሎች አገልግሎቶች የሚውል የጂኦተርማል ሀብት ነው፤

፲/ "አግባብ ያለው አካል" ማለት ሐረጉ የተጠቀሰበት ድንጋጌ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ በሕግ ኃላፊነት እና ሥልጣን የተሰጠው መንግሥታዊ አካል ነው፤

፲፩/ "አላቂ ዕቃዎች" ማለት ለጂኦተርማል ሥራ የሚያስፈልጉና በጂኦተርማል ሥራው ወቅት በጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም የሚተኩ ኬሚካሎች፣ ሲሚንቶን ጨምሮ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በመመሪያ አላቂ ዕቃዎች ብሎ የሚሰይማቸው ናቸው፤

፲፪/ "ሰነድ" ወይም "ሪከርድ" ማለት የኤሌክትሮኒክስ ጽሑፎችን ወይም ሪከርዶችን ጨምሮ ማንኛውም ጽሑፍ ወይም ሪከርድ ነው፤

፲፫/ "መቆፈር" ማለት ለጂኦተርማል ሥራ የሚደረግ የጉድጓድ ቁፋሮ ነው፤

6/ "geothermal resource area" means any land where geothermal resources have been discovered or is believed to be a source of geothermal resources and is so designated by the licensing authority by public notice;

7/ "business organization" shall have the meaning provide for under the Commercial Code of Ethiopia;

8/ Grade I geothermal resources" means a type of geothermal resources capable to generate electric power and to provide services such as direct heating and combined heat and power;

9/ "Grade II geothermal resources" means a type of geothermal resources used for the purposes such as direct heating, agricultural and industrial applications and recreational bathing and medicinal purposes, but excludes the purposes of generating electricity;

10/ "competent body" means any government organ empowered by law with responsibility and authority related to the subject specified in the provisions in which the phrase is used;

11/ "consumables" means anything may be utilized for geothermal operations and that is expendable or may be replaced during service such as chemicals, other items including cement that the licensing authority may, by directive, designate as consumables;

12/ "document" or "record" means any writing or record, including electronic writings or records;

13/ "drilling" means an operation in which a well is drilled for the purposes of geothermal operations;

፲፬/ “የምርመራ ፈቃድ” ማለት የጂኦተርማል ሀብት መኖሩንና የሀብቱን መጠንና የኢኮኖሚ ጥቅም ለማረጋገጥ ሲባል ጉድጓዶችን መቆፈርን እንዲሁም ለጉድጓድ ፍተሻ ሲባል የጂኦተርማል ፈሣሾችን መልቀቅን ጨምሮ ዝርዝር የጂኦሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪና የጂኦፊዚክስ ጥናቶችን በማከናወን የጂኦተርማል ሀብትን መጠን፣ አቀማመጥ፣ ባሕርያትና ወሰን ለማረጋገጥ የሚረዱ ሥራዎችን ለማካሄድ መብት የሚሠጥ ፈቃድ ሲሆን የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ፣ የሀብት መጠንና የአዋጭነት ጥናቶችን ማጥናትና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድንም ይጨምራል፤

፲፭/ “ኮር” ማለት በቁፋሮ ከጉድጓድ የሚወሰድ ጠጣር የአለት ናሙና ነው፤

፲፮/ “ማመንጨት” ማለት በኢነርጂ አዋጅ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፤

፲፯/ “መንግሥት” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሲሆን እንደ አግባቡ ክልል መንግሥታትንም ይጨምራል፤

፲፰/ “የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት ክልል” ማለት የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት ክልል ተብሎ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሕዝብ ማስታወቂያ የተሰየመ አካባቢ ነው፤

፲፱/ “መሬት” ማለት ከመሬት በታችም ይሁን በላይ የንብረት አገልግሎት መብት ወይም ጥቅም የተገኘበት በማንኛውም ዓይነት ይዞታ ሥር የሚገኝ መሬት ሲሆን በውሃ የተሸፈነ መሬትንም ያካትታል፤

፳/ “ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ነው፤

፳፩/ “የሕዝብ ማስታወቂያ” ማለት ሰፊ ተደራሽነት ባለው መገናኛ ብዙሀን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተቱ መሠረታዊ ጉዳዮችን ይፋ ማድረግ ነው፤

፳፪/ “የቅኝት ፈቃድ” ማለት አንድ ቦታ የጂኦተርማል ሀብት ሊኖረው እንደሚችል ለማረጋገጥ ሲባል የጂኦሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪና የጂኦፊዚክስ ባሕርያቱን ለማጥናት የሚያስችሉና በአካባቢው

14/ “exploration license” means a license that gives the right to undertake activities that help to establish the dimensions, position, characteristics and extent of geothermal resources by detailed geological, geochemical and geophysical studies including the drilling wells, discharge of geothermal fluids for the purpose of well testing, and also includes conducting environmental and social impact assessment, resource assessment and feasibility studies and other related activities in order to establish the existence of geothermal resources and to determine their extent and economic value;

15/ “core” means solid rock sample taken out from underground through drilling;

16/ “generation” shall have the meaning provided for under the Energy Proclamation;

17/ “Government” means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes States where appropriate;

18/ “known geothermal resource area” means an area designated by the licensing authority by public notice as a known geothermal resource area;

19/ “land” means any land under whatever tenure held and any servitude, right or privilege in or over land and includes land covered with water;

20/ “licensing authority” means the Ethiopian Energy Authority;

21/ “public notice” means publication of the substantive material addressed in this Proclamation through widely accessible mass media or electronic media;

22/ “reconnaissance license” means a license that gives right to undertake surface exploration activities without environmental impact and that are intended to assess geological,

ተፈጥሮ ላይ ተጽዕኖ የሌላቸውን የመሬት ላይ የምርመራ ሥራዎችን ለማካሄድ መብት የሚሠጥ ፈቃድ ሲሆን ጉድጓድ መቆፈርን አያካትትም፣

፳፫/ “ሪኢንጀክሽን” ማለት የጂኦተርማል ፈሳሽን በጉድጓድ አማካኝነት ከመሬት በታች መልሶ መጨመር ነው፣

፳፬/ “መሠረዝ” ማለት ባለፈቃዱ ፈቃዱን በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አስገዳጅነት እንዲመልስ ማድረግ ነው፣

፳፭/ “መመለስ” ማለት በባለፈቃዱ በፈቃደኝነት ፈቃዱን ወይም ከፈቃዱ ክልል ውስጥ የተወሰነን ቦታ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መመለስ ነው፣

፳፮/ “የሙቀት መለኪያ ጉድጓድ” ማለት የጂኦሳይንስ ትሬክ ወይም ከሙቀት ጋር የተያያዘ መረጃ ለማግኘት ሲባል የሚቆፈር ማንኛውም ጉድጓድ ነው፣

፳፯/ “መቋረጥ” ማለት ከፈቃድ መሠረዝ፣ መነጠቅ ወይም መመለስ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ባለፈቃዱ የነበረው መብት ሲያበቃ ነው፣

፳፰/ “ማስተላለፍ” ማለት የጂኦተርማል ፈቃድ ወይም ከፈቃዱ ጋር ተያያዥ ሀብትን መሸጥ፣ በዕዳ ማስያዝ፣ ማውረስ፣ መዳረግ ወይም በሌላ መንገድ ባለቤትነትን ማስተላለፍ ነው፣

፳፱/ “ጉድጓድ” ማለት የጂኦተርማል ሀብት ለመፈለግ ወይም ለማምረት ወይም የጂኦተርማል ሀብቱን ሪኢንጀክት ለማድረግ ወይም ለመከታተል በማን ኛውም መሬት ላይ ተቆፍሮ የተጠናቀቀ ጉድጓድ ነው፣

፴/ “የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ” ማለት የጂኦተርማል የሀብት መጠንና የአዋጭነት ጥናቶችን ለማጥናት፣ ከፍተኛ ደረጃ የጂኦሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪና የጂኦፊዚክስ ጥናቶችን ለማካሄድ፣ የምርት፣ የሪኢንጀክሽንና የክትትል ጉድጓዶችን ለመቆፈር፣ የእንፋሎት መስክን ለማልማት፣ የጂኦተርማል ሀብትን ከመሬት ሥር ለማውጣትና ለመጠቀም መብት የሚሠጥ ፈቃድ ነው፣

geochemical and geophysical characteristics for the purpose of determining whether a land may have geothermal resources, but not including drilling activities;

23/ “re-injection” means a process of returning to the subsurface geothermal fluids through a well;

24/ “revocation” means a return of a license from the licensee by the order of the licensing authority;

25/ “surrender” means a voluntary return of a license or any portion of the license area by a licensee to the licensing authority;

26/ “temperature gradient well” means any well drilled expressly for the acquisition of geo-scientific or temperature-related data;

27/ “termination” means cessation of rights of a licensee by an act, including expiration, revocation or surrender of a license;

28/ “transfer” means a sale, encumbrance, inheritance, assignment or any other change in ownership of a geothermal resource license or related asset;

29/ “well” means any hole drilled and completed on any land which is made for the discovery or production of geothermal resources or for re-injecting or monitoring geothermal resources;

30/ “geothermal well-field development and use license” means a license that gives right to undertake geothermal resource assessment and feasibility studies, advanced geological, geochemical and geophysical studies, drilling of production, re-injection and monitoring wells, steam-field development, extraction and use of geothermal resources;

፴፩/ "የሥራ ፕሮግራም" ማለት ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የጂኦተርማል ቅኝት ፈቃድ እና የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም የጂኦተርማል ምርመራ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለማደስ እንደቅድመ ሁኔታ መቅረብ ያለበት የሥራ ዝርዝር እና የወጪ ዕቅድ ነው፣

፴፪/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፣

፴፫/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠ አካል ነው፣

፴፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በሚካሄዱ የጂኦተርማል ሀብት ልማት ሥራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፬. ዓላማ

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ የሀገሪቱ የጂኦተርማል ሀብት ሥርዐትና ዘላቂነት እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃን ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ መልማቱን ማረጋገጥ፣

፪/ ከጂኦተርማል ኃይል ለአገር ውስጥ እና ለውጭ አገር ፍጆታ የሚውል ኤሌክትሪክ ማመንጨትንና ማቅረብን መደገፍ፣

፫/ የደረጃ II ጂኦተርማል ሀብትን ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውልበትን ሁኔታ ማራመድ፣

፬/ በጂኦተርማል ሀብት ልማት ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶች መብቶችን የማረጋገጥ፣ እና

፭/ በኢትዮጵያ ቀጣይነት ያለው ከካርቦን ነፃ የሆነ ኢኮኖሚን ማበረታታት፡፡

31/ "work program" means the program of work showing details of the work and expenditure as may be further defined in pursuant to this Proclamation and regulation and directive issued hereunder and required as a precondition for granting a reconnaissance and geothermal well-field development and use licenses, and granting or renewing exploration license;

32/ "State" means any national regional state specified under Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

33/ "person" means any natural or juridical person;

34/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall apply to geothermal resources development activities within the territory of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

## 4. Objectives

This Proclamation shall have the following objectives:

1/ ensuring that the country's geothermal resources are developed in an orderly, sustainable and environmentally responsible manner;

2/ supporting the generation and delivery of electricity from geothermal energy for local consumption and export;

3/ promoting the use of Grade II geothermal resources for various uses;

4/ ensuring security of tenure for all investors in respect of geothermal resources development operations; and

5/ encouraging a sustainable, carbon-neutral economy in Ethiopia.

## ክፍል ሁለት
## ስለ ጂኦተርማል ሀብት ልማት ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፭. ውጤታማ የመሬትና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም**

፩/ አዋጭና ከዚህ አዋጅ ጋር የሚስማማ እስከሆነ ድረስ ለጂኦተርማል ሀብት ልማት በሚሰጥ የፈቃድ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ከጂኦተርማል ፈቃዱ ጎን ለጎን ጥቅም ላይ እንዲዉሉ አግባብ ባለው አካል ሊወሰን ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ሥራ በሚካሄድበት የፈቃድ ክልል ውስጥ ጂኦተርማልን የማይመለከቱ ሌሎች የልማት ሥራዎች ጎን ለጎን የሚካሄዱበትን አሠራር በተቻለ መጠን መደገፍ አለበት።

**፮. የሀብት ጥበቃና ዘለቄታዊነት**

የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ያለው ባለፈቃድ ተገቢነት ያለውና ከአካባቢ ብክለት የጸዳ አሠራር የመከተል ግዴታ ያለበት ሲሆን የጂኦተርማል ሀብቱ ዘለቄታዊነት መጠበቁን ለማረጋገጥ ሲባል ከጂኦተርማል ኢንዱስትሪ ምርጥ አሠራርና ከጂኦተርማል ሀብቱ ባሕርያት ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ የጂኦተርማል ፈሣሾች ሪኢንጄክሽንን መተግበር አለበት።

**፯. መሬትን ለጂኦተርማል ሥራዎች ስለመከለል**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሬት ለጂኦተርማል ሥራዎች ክፍት ይሆናል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ማናቸውም መሬት የታወቀ የጂኦተርማል ክልል ነው ብሎ ሊሰየም ይችላል፡፡ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የታወቀ የጂኦተርማል ክልልን መጠን እና ቅርጽን ለመወሰን ከሌሎች ሁኔታዎች በተጨማሪ፦

ሀ) እንዲከለል ሀሣብ የቀረበበትን አካባቢ የታወቀ የጂኦሎጂካል፣ ጂኦኬሚካል እና

## PART TWO
## GENERAL PROVISIONS ON GEOTHERMAL RESOURCE DEVELOPMENT

**5. Productive Use of Land and Other Resources**

1/ The competent body may decide that other natural resources in the geothermal resource license area may be developed, in so far as feasible and in a manner consistent with this Proclamation and under the laws applicable to them.

2/ The licensing authority shall, to the extent feasible, support the coexistence of non-geothermal development activities within the license area of geothermal operations.

**6. Resource Conservation and Sustainability**

Geothermal well-field development and use licensee shall avoid unreasonable waste affecting environment and promote the sustainability of geothermal resources, and to that end, the license shall practice re-injection of geothermal fluids when re-injection is consistent with geothermal industry best practices and the characteristics of the geothermal resource.

**7. Reservation of Land for Geothermal Operations**

1/ Without prejudice to sub-articles (3) and (4) of this Article, any land in Ethiopia shall be available for geothermal operations.

2/ The licensing authority may, by public notice, designate an area as a known geothermal resources area. In designating the size and configuration of the known geothermal resources area the licensing authority shall, among other considerations, take into account:

a) known geological, geochemical and geophysical characteristics of the area

ጂኦፊዚካል ባህርያትን፤ እና

ለ) የጂኦተርማል ሀብቱ የሚገኝበት መሬት በወቅቱ እየሰጠ ያለውንና ወደፊት ሊሰጥ የሚችለውን ሌላ ጠቀሜታ፣ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ማናቸውም መሬት የጂኦተርማል ሥራ የማይካሄድበት ነው ብሎ መከለል ይችላል፡፡ ሆኖም ይህን የመሰለው ክልከላ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ በተሰጠው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመካስ መብት ይኖረዋል።

፬/ ማንኛውም ሰው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሥፍራዎች ላይ የጂኦተርማል ሥራዎች ፈቃድ አይሰጠ ውም፡-

ሀ) ለመቃብርና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በተከለሉ ሥፍራዎች፤

ለ) የቅድመ ታሪክ ቅሪቶች ባሉባቸው ወይም ብሔራዊ መታሰቢያዎች በቆሙባቸው ሥፍራዎች፤

ሐ) ለመሠረተ ልማት አውታሮች በተከለሉ ቦታዎች፤

መ) ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ወይም ለብሔራዊ ፓርክ በተከለሉ ሥፍራዎች፤

ሠ) አግባብ ያለው አካል ካልፈቀደ በቀር ከመንደሮች፣ ከከተማዎች ወይም ከውኃ ማጠራቀሚያዎች ወይም ግድቦች በአምስት መቶ (፭፻) ሜትር ክልል ውስጥ፤ እና

ረ) በሌላ ሕግ በተከለከሉ ቦታዎች፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የሕዝብ ማስታወቂያ በሥራ ላይ በዋለበት ቀን ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ በተሰጠበት እና የፀና የኃይል ግዥ ስምምነት ባለው መሬት መጠንና ቅርጽ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፮/ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ተገቢው የማካካሻ እርምጃ ተወስዶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ወይም (፬) መሠረት የተከለለ ማንኛውም ሥፍራ ለጂኦተርማል ሥራ ክፍት እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

proposed for designation; and

b) the existing and potential uses of the land overlying the geothermal resources.

3/ The licensing authority may by public notice, upon a determination that such a reservation would be in the best interests of the public, reserve any land, within which geothermal operations shall not be conducted; provided, however, that if such prohibition is detrimental to a person holding license under this Proclamation, the person shall have the right to compensation according to the relevant laws.

4/ No person shall be granted a geothermal operations license over an area:

a) which is reserved for cemeteries and religious sites;

b) contains archaeological remains or national monuments;

c) which is reserved for infrastructure area;

d) which is within areas reserved for natural habitats or national parks;

e) which is within five hundred (500) meters from the boundary of a village, city, water reservoir or dam without permission of the competent body; and

f) which is protected by any other law of the country.

5/ A public notice issued pursuant to sub-article (2) of this Article shall not affect the size and configuration of the land that, on the date of the public notice, is subject to a geothermal license granted prior to the coming into force of this Proclamation with a valid power purchase agreement.

6/ The Government may, upon a determination that it is in the best interest of the public, authorize the availability of any protected area under sub-articles (3) or (4) of this Article for geothermal operations, upon providing appropriate

፰. በመንግሥት ስለሚካሄድ የጂኦተርማል ሥራ

፩/ መንግሥት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ዕድገት ወሳኝ ሚና የሚኖራቸውን የጂኦተርማል ሥራዎች በራሱ ወይም ከሌሎች ባለሀብቶች ጋር በቅንጅት ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድን አወዳድሮ ለመስጠት የሚያስችለው በቂ መረጃ እንዲኖረው ለማስቻል መንግሥት የጂኦተርማል ሀብት ፍለጋ እና ልማት ሥራዎች ያካሂዳል፡፡

፱. ስለ ጂኦተርማል ሀብት መዝገብ

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ሀብት መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

፪/ በጂኦተርማል ሀብት መዝገብ ውስጥ የፈቃድ ማመልከቻዎችና ፈቃድን ለመስጠት፣ ለመከልከል ወይም ለመሠረዝ የተሰጡ ውሳኔዎች፣ የይግባኝ ሪከርዶችና በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰኑ የጽሑፍ ሰነዶች ይመዘገባሉ፡፡

፫/ ከፈቃድ ጋር የተገናኙና በግል የተካሄዱ ግብይቶችን፣ ማስተላለፍን፣ በዕዳ መያዝን፣ በውርስ ማስተላለፍን የሚመለከቱ ሰነዶች ስምምነቱ ከተከናወነ ወይም ህጋዊነትን ካገኘ በኋላ ባሉት በዘጠና (፺) ቀናት ውስጥ መብቱን ባገኘው ሰው አማካይነት ቀርበው መመዝገብ አለባቸው፡፡ ለምዝገባ በወቅቱ ያልቀረቡ ስምምነቶች በሕግ ፊት ዋጋ አይኖራቸውም፡፡

፬/ የጂኦተርማል ሀብት መዝገብ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል፡፡

፲. ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ስለማሳወቅ

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ በጂኦተርማል ሀብት መዝገብ ከመዘገበ በኋላ ጥያቄ የቀረበበትን ቦታ የጂኦግራፊ ኮኦርድኔት በመጥቀስ ሰፊ ተደራሽነት ባለው የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ሦስተኛ ወገኖች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

compensatory arrangements, if any.

**8. Government Geothermal Operations**

1/ The Government may, either by itself or in partnership with other investors, undertake geothermal operations that have crucial role for the country's economic and social development.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article the Government shall undertake geothermal resource exploration and development activities to provide sufficient data to the licensing authority to facilitate the granting of license for well-filed development and use license on a competitive basis.

**9. Register of Geothermal Resources**

1/ The licensing authority shall establish and maintain a register of geothermal resources.

2/ Applications for licenses and decisions for granting, denying or revoking licenses, records of appeals and other written documents determined by this Proclamation and regulation and directive issued hereunder shall be registered in geothermal resources register.

3/ Instruments involving private transactions, transfers, encumbrances, and inheritance of interests in licenses, shall be presented for registration by the person who acquired the rights within ninety (90) days after the conclusion of the agreement or to get legality; if an agreement is not timely presented for registration it shall be null and void.

4/ The geothermal resources register shall be open to the public.

**10. Notification of Interested Parties**

1/ The licensing authority shall, after registering an application in the register of geothermal resources, publicize it to third parties through public mass media having wider access by specifying the geographic coordinate of the area to which application is lodged.

፪/ ፈቃድ እንዳይሠጥ ተቃውሞ የሚያቀርብ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥያቄ የቀረበበት ቦታ በመገናኛ ብዙሃን እንዲታወቅ በተደረገ በአሥራ አምስት (፲፭) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ያቀረበ እንደሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጉዳዩ ላይ በሚመለከታቸው ወገኖች መካከል ድርድር እንዲጀመር ያደርጋል፡፡

፫/ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች የቀረበውን ተቃውሞ አስመልክቶ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ድርድሩ እንዲጀመር ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በስልሣ (፷) ቀናት ውስጥ መስማማት ካልቻሉ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ካዳመጠ በኋላ በአሥራ አምስት (፲፭) የሥራ ቀናት ውስጥ የቀረበውን ተቃውሞ የመቀበል ወይም ያለመቀበል ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን

**፲፩. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር**

ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የጂኦተርማል ሀብት ልማት ኢንቨስትመንትን ለማሣደግ የሚረዱ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፤

፪/ የጂኦተርማል ሀብት ልማትን የሚመለከቱ ተግባራት በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መከናወናቸውን የማረጋገጥ፤

፫/ የጂኦተርማል ሀብት ልማትን በማሳደግ እና ባለፈቃዶች ኃላፊነቶቻቸውን እንዲወጡ በማድረግ መካከል የሚኖርን ወይም ሊከሰት የሚችል የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ ተገቢ እርምጃ የመውሰድ፤

፬/ በደረጃ I እና ደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃዶችን የመስጠት ወይም የመከልከል የተሰጡ ፈቃዶችን የማደስ፣ የማገድ፣ የማራዘም እና የመሠረዝ፤

፭/ ለጂኦተርማል ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ሥራ እና ለጂኦተርማል ቴክኒክ ነክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

2/ If any person objects to the granting of the license within fifteen (15) days from the date of the publicity of the area requested for license under sub-article (1) of this Article, the licensing authority shall initiate negotiations between the concerned parties to resolve the objection.

3/ If the parties fail to resolve the objection amicably within sixty (60) days starting from the date fixed by the licensing authority to start the negotiation, the licensing authority shall hear the presentations of both parties and pass decision within fifteen (15) working days either by upholding or rejecting the objection.

## PART THREE
## LICENSING AUTHORITY

**11. Powers and Duties of the Licensing Authority**

The licensing authority shall have the powers and duties to:

1/ promote conditions necessary for the development of geothermal resources investment activities;

2/ ensure the compliance of geothermal resources development activities with this Proclamation and the regulations and directives issued hereunder;

3/ take appropriate measures to prevent an actual or perceived conflict of interest between the promotion of the development of geothermal resources and compliance responsibilities of licensees;

4/ issue or deny, renew, suspend, extend, revoke and terminate geothermal operations license issued on Grade I and Grade II geothermal resources operation;

5/ issue certificates of competency for consultancy and geothermal works in the geothermal sector;

፮/ የጂኦተርማል ፈሳሽና ተያያዥ ውጤቶች ወደ ውጪ እንዲላኩ ፈቃድ የመስጠት ወይም የመከልከል፣

፯/ አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር የጂኦተርማል ተረፈ ምርት ጥቅም ላይ እንዲውል ወይም እንዲሸጥ የመፍቀድ፣

፰/ የፈቃድ ክልል በጨረታ ወይም በማመልከቻ የሚሰጥበትን ሁኔታ የመወሰን፣

፱/ በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱ ግዴታዎችን ለመወጣት አስፈላጊው የገንዘብ ምንጭ፣ የቴክኒክ ብቃትና ልምድ ያለው መሆኑን የማረጋገጥ፣

፲/ አንድን አካባቢ የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት መገኛ ክልል ብሎ የመሰየም፣

፲፩/ በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱ መረጃዎችን እና ሪከርዶችን የመቀበል፣

፲፪/ የጂኦተርማል ሥራዎች በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ፣ መመሪያና አግባብ ባላቸው ስምምነቶች መሠረት መካሄዳቸውን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ፣

፲፫/ በመንግሥት በሚወጣ ተመን መሠረት የፈቃድና ሌሎች ክፍያዎችን የመሰብሰብ፣

፲፬/ አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር የጂኦተርማል ሥራዎች ከኢትዮጵያ የአካባቢ፣ የጤና እና የደህንነት ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣

፲፭/ ከጂኦተርማል ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የጤ ናና የደህንነት ደረጃዎችን፣ የጉድጓድ ቁፋሮ ኮዶችን፣ የቁጥጥር መመሪያዎችንና ሌሎች መሰል ኮዶችን የማውጣትና አፈፃፀማቸውንም የመቆጣጠር፣

፲፮/ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመተባበር፡፡

6/ authorize or deny permission for the export of samples of geothermal fluids and related products;

7/ authorize the use and sale of geothermal by-products in consultation with the competent body;

8/ determine whether a license on certain license area shall be given through competitive bid or application;

9/ ensure that any licensee has the necessary financial resources, technical capability and experience to fulfill the obligations provided under license in accordance with this Proclamation;

10/ designate an area as a known geothermal resource area;

11/ receive information and records specified in this Proclamation and regulations and directives issued hereunder;

12/ inspect to ensure that geothermal operations are carried out in accordance with this Proclamation and regulation and directive issued hereunder and applicable licenses agreements;

13/ collect license fees and other payments pursuant to rates approved by the Government;

14/ ensure, in collaboration with the competent body, that geothermal operations comply with environmental, health and safety laws of Ethiopia;

15/ issue health and safety standards, drilling code of practices, inspection guidelines, and other codes and standards related to geothermal operations and supervise the implementation of same;

16/ collaborate with competent bodies for the implementation of this Proclamation.

## ክፍል አራት

## ስለ ፈቃዶች እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶች

**፲፪. የፈቃድ አስፈላጊነት**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ተገቢውን ፈቃድ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሳያገኝ የጂኦተርማል ሥራ ማካሄድ አይችልም፡፡

**፲፫. የፈቃድ ዓይነቶች**

፩/ ማንኛውም አመልካች በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ካሟላ የሚከተሉት የጂኦተርማል ሥራ ማካሄድ የሚያስችሉ ፈቃዶችን በደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ላይ ሊሰጡት ይችላሉ፦

ሀ) የቅኝት ፈቃድ፤

ለ) የምርመራ ፈቃድ፤ እና

ሐ) የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ፡፡

፪/ በደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ እና ዝርዝር ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ክልሎች ሙቀቱ ከአንድ መቶ ሀያ (፩፻፳) ዲግሪ ሴንቲግሬድ በማይበልጥ እና መጠኑ በዓመት ከሁለት ሚሊዮን (፪ ሚሊዮን) ሜትር ኪዩብ በማይበልጥ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ይሰጣሉ፡፡

**፲፬. የቅኝት ፈቃድ**

፩/ የቅኝት ፈቃድ የብቻ የሆነ መብት የማያስገኝና ያለውድድር የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

፪/ የቅኝት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለፀው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፣ ሆኖም ይህ ጊዜ ከሃያ አራት (፳፬) ወር በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

፫/ የቅኝት ፈቃድ አይታደስም፡፡

## PART FOUR

## LICENSES AND CERTIFICATES OF PROFESSIONAL COMPETENCY

**12. Requirement of License**

No person, may undertake geothermal operations without having appropriate license from the licensing authority pursuant to this Proclamation.

**13. Types of Licenses**

1/ The licensing authority may grant the following geothermal operation licenses on Grade I geothermal resources to any applicant that meets the requirements prescribed in this Proclamation and regulation and directive issued hereunder:

a) reconnaissance license;

b) exploration license; and

c) geothermal well-field development and use license.

2/ The manner and details of granting geothermal operations license on Grade II geothermal resources shall be determined by regulation and directive to be issued for the implementation of this Proclamation.

3/ Without prejudice to sub-articles (1) and (2) of this Article, Regional States shall grant operation licenses license on Grade II geothermal resource the temperature of which do not exceed one hundred twenty (120) degree centigrade and volume not exceeding two million (2,000,000) meter cube per year.

**14. Reconnaissance License**

1/ A reconnaissance license shall be issued on a non-exclusive and non-competitive basis.

2/ A reconnaissance license shall be valid for the period specified in the license; provided, however, such period shall not exceed twenty four (24) months.

3/ A reconnaissance license shall not be renewable.

፬/ የቅኝት ፈቃድ ያዥ የቅኝት ክልል በምርመራና በጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ሥር ያልተያዘ ከሆነ እና በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የተገለፁ አስፈላጊ መስፈርቶችን የሚያሟላ ከሆነ የምርመራ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፡፡

፭/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቅኝት ፈቃድ ሥር የነበረን ክልል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው የምርመራ ወይም የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ የሰጠ ከሆነ ይህንኑ ለቅኝት ፈቃድ ያዡ ማስታወቅ አለበት፡፡

**፲፭. <u>የምርመራ ፈቃድ</u>**

፩/ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የምርመራ ፈቃድ የሚሰጠው፦

ሀ) በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ የሥራ ዕቅድ እና የአካባቢና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ላቀረበ፣

ለ) የታሰበውን የምርመራ ሥራ በቀረበው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን እና አስፈላጊው የቴክኒክ ችሎታ ያለው መሆኑን ላረጋገጠ፣

ሐ) ከዚህ በፊት የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ፈቃድ ግዴታዎች ላልጣሰ አመልካች ይሆናል፡፡

፪/ የምርመራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለፀው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፣ ሆኖም ይህ ጊዜ ከአምስት (፭) ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

፫/ የምርመራ ፈቃድ እያንዳንዱ ከአንድ (፩) ዓመት ለማይበልጥ ለሁለት ጊዜ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ሲያገኝ ሊታደስ ይችላል፤ ሆኖም ለሁለተኛ ጊዜ የታደሰ የምርመራ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃ ይሠረዛል፡፡

4/ The holder of a reconnaissance license, may apply for a geothermal exploration license if he meets the requirements specified in this Proclamation and regulation and directive issued hereunder; and provided that the area applied for is not under an exploration or geothermal well-field development and use license and that.

5/ The licensing authority shall notify a holder of reconnaissance license, if an exploration or geothermal well-field development and use license has been granted to another person for the whole or part of the reconnaissance license area.

**15. <u>Exploration License</u>**

1/ An exclusive exploration license shall be granted to an applicant who:

a) has submitted work program and environmental and social impact assessment and got approval from the licensing authority;

b) has demonstrated financial capability or access to the financial resources and the technical ability to conduct the proposed exploration in accordance with the approved work program;

c) is not in breach of any obligation of a geothermal operation license, if any.

2/ An exploration license shall be valid for an initial period specified in the license; provided, however, such period shall not exceed five (5) years.

3/ An exploration license may be renewed twice, each for a period not exceeding one (1) year upon approval by the licensing authority; provided, however, that an exploration license shall be terminated at the end of the second renewal period.

፬/ ባለፈቃዱ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች አሟልቶ ከፈፀመ፣ ለዕድሳት የሚጠየቁ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ካሟላና ይህን አዋጅ፣ አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈፀመ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት መንግሥት ፈቃዱን ሊያድስለት ይችላል፡፡

**፲፮. የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ**

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ የሚሰጠው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ለሚያሟላ አመልካች ይሆናል፡-

ሀ) በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ የሥራ ዕቅድ፣ የአዋጭነት ጥናትና የአካባቢ እና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ላቀረበ፤

ለ) ሕጋዊ የኃይል ግዥ ስምምነት ላለው፤

ሐ) የታሰበውን ሥራ በቀረበው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅምና አስፈላጊው የቴክኒክ ችሎታ ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን ላረጋገጠ፤

መ) ከዚህ በፊት የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ፈቃድ ግዴታዎች ላልጣሰ፡፡

፪/ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለፀው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከሃያ አምስት (፳፭) ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም።

፫/ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ መንግሥት በሚመቸው መንገድ የጂኦተርማል ሀብት ልማቱን ሊያስቀጥል ይችላል፡፡

4/ Government may renew the license pursuant to sub-article (3) of this Article; provided that the licensee has fulfilled the obligations specified in the license, meets all the requirements in connection with application for the renewal and is not in breach of any provision of this Proclamation, regulations or directives issued hereunder which constitute grounds for suspension or revocation of the license.

**16. Geothermal Well-field Development and Use License**

1/ The Authority shall grant a license for an exclusive geothermal well-field development and use to an applicant who satisfies the following conditions:

a) who has submitted work program, feasibility study and environmental and social impact assessment and got approval from the licensing authority;

b) has acquired a valid power purchase agreement;

c) has demonstrated financial capability or access to the financial resources and the technical ability to conduct the proposed exploration in accordance with the approved work program;

d) is not in breach of any obligation of a geothermal operation license, if any.

2/ A geothermal well-field development and use license shall be valid for an initial period specified in the license; and such period shall not exceed twenty five (25) years.

3/ When the validity period of the geothermal well-field development and use license expires, Government may continue the development of the geothermal resource as it finds feasible.

፬/ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ባለፈቃድ በደረጃ I ጂኦተርማል ሀብት ላይ የኃይል ማመንጨት ተግባርን ብቻ የማካሄድ ወይም በተጓዳኝ ጥቅም ላይ የዋለ የጂኦተርማል ሀብትን ለራሱ የመጠቀም ወይም በሽያጭ መንግስት እንዲጠቀምበት የማድረግ መብት አለው፡፡

፭/ አግባብነት ያላቸውን የኢነርጂ ሕግ ድንጋጌዎች የሚያሟላና በደረጃ I ጂኦተርማል ሀብት ላይ የኃይል ማመንጨት ተግባር ለማካሄድ ብቁ የሆነ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ባለፈቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ ሲያቀርብ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፮/ በደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ባለፈቃድ በሀገሪቱ የኢነርጂ እና የኢንቬስትመንት ሕግ መሠረት ከጂኦተርማል ሀብት ኤሌክትሪክ የማመንጨት እና ያመነጨውን ኤሌክትሪክ አግባብ ላለው አካል የመሸጥ ግዴታ አለበት፡፡

፲፯. <u>ፈቃድን በውድድር ስለመስጠት</u>

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሙከራ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራዎች ተከናውነውና የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ለመስጠት በሚያስችል ደረጃ የጂኦተርማል ሀብት መኖሩ የተረጋገጠ የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት ክልልን በማወዳደር የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተወሰነን ክልል የሚመለከት የምርመራ ፈቃድ ማመልከቻ የቀረበለት እንደሆነ የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ፍላጎት ያላቸው ሌሎች ሰዎች የሕዝብ ማስታወቂያው በወጣ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ማመልከቻ ለቀረበበት ቦታ የቴክኒክ ብቃትንና የገንዘብ አቅምን በመመዘኛነት በመጠቀም እንዲወዳደሩ መጋበዝ አለበት፡፡

4/ A geothermal well-field development and use licensee shall have the right to undertake power generation activities on Grade I geothermal resources, either as a standalone operation or combined with sale of used geothermal resource for direct use by Government, or for self-use.

5/ A geothermal well-field development and use licensee who qualifies for power generation activities on Grade I geothermal resources shall be granted a license to generate electricity upon application to the licensing authority, provided that the licensee demonstrates compliance with the relevant provisions of the Energy Law.

6/ The holder of a geothermal well-field development and use license on a Grade I geothermal resource shall have the obligation to generate and to sell the electricity generated from geothermal resources to the competent body as promulgated in the relevant Energy and Investment Laws of the country.

**17. <u>Competitive Award of Licenses</u>**

1/ The licensing authority may grant a geothermal well-field development and use license on a competitive basis for a known geothermal resource area, where exploration activities have been conducted for the area at least to the level of test drilling and the existence of geothermal resources have been confirmed to the degree sufficient to grant a well-filed development and use license.

2/ If the licensing authority receives an application for an exploration license for an area, it shall, through a public notice, invite other interested persons to apply within thirty (30) days from the date of publicity for the purpose of competitive award of the same area based on technical ability and financial capacity criteria of the applicants.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ ያልቀረበለት እንደሆነ በቅድሚያ የተቀበለውን ማመልከቻ ያስተናግዳል፡፡

**፲፰. ስለማመልከቻ ሥነ–ሥርዓት**

ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በፍጥነትና በብቃት የሚስተናገዱበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥነ–ሥርዓቶች፣ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችና የጊዜ ገደቦች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ፡፡

**፲፱. ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስላለመሆን**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ፈቃድ ማግኘት አይችሉም፡-

ሀ) ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት መክሠሩ የተረጋገጠ ማንኛውም ሰው፤

ለ) የማፍረሱ ሂደት የንግድ ማኅበሩን እንደገና ለማቋቋም ወይም ከሌላ ኩባንያ ጋር ለማዋሃድ እስካልሆነ ድረስ በመፍረስ ላይ ያለ የንግድ ማኅበር፤

ሐ) ከማመልከቻው ጋር የተሳሳተ መረጃ ሆን ብሎ ያቀረበ ወይም ማመልከቻውን አስመ ልክቶ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለሚሰጠው ውሣኔ አስፈላጊ የሆነ መረጃ ሆን ብሎ ያላቀረበ ሰው፤

መ) ቀድሞ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የተሳሳተ መረጃ ሆን ብሎ ያቀረበ ወይም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለሚያካሄደው የሪፖርት ግምገማ አስፈላጊ የሆነ መረጃ ሆን ብሎ ያላቀረበ ሰው፡፡

፪/ በማጭበርበር ወይም ለፈቃድ ሰጪው ባለሥ ልጣን አስፈላጊ የሆነ መረጃን ሆን ብሎ ባለማቅረብ ፈቃዱ የተሠረዘበት ባለፈቃድ ፈቃዱ ከተሠረዘበት ቀን አንስቶ ለአሥር (፲) ዓመታት ማንኛውንም ዓይነት ፈቃድ ማግኘት አይችልም፡፡

**፳. ስለሥራ ፕሮግራም**

፩/ ማንኛውም ዓይነት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚያ መለክት ሰው ከማመልከቻው ጋር የሥራ ፕሮግራሙን፣ በጀቱን እና በፈቃዱ የተሸፈኑ ተግባራትን የሚመለከቱ ዝርዝር ሥራዎችን የያዘ የሥራ ፕሮግራም ማቅረብ አለበት፡፡

3/ If the licensing authority receives no application pursuant to sub-article (2) of this Article, it shall consider the application of the initial applicant.

**18. Application Procedure**

The procedures, requirements and timelines for applications shall be provided in regulation to be issued pursuant to this Proclamation to ensure expeditious processing of applications for licenses.

**19. Ineligibility for License**

1/ Without prejudice to of Article 13 (1) of this Proclamation no license shall be granted to:

a) a person who is declared bankrupt by the court having jurisdiction;

b) a business organization that is in liquidation, other than liquidation which forms a part of a scheme for the reorganization or merger with another business organization;

c) a person who has knowingly provided false information in its application; or knowingly failed to provide information to the licensing authority for decision with respect to his application;

d) a licensee who has knowingly provided false information or knowingly failed to provide information to the licensing authority for the review of required reports.

2/ A licensee whose license is revoked due to fraudulent misrepresentation, or knowingly fails to provide material information required by the licensing authority shall not be granted any license for ten (10) years starting from the date of revocation of the previous license.

**20. Work Program**

1/ Any person lodging application to obtain any type license shall submit his application accompanied with a work program, including budget, detailing the program of work for each activity covered by the license.

፪/ ባለፈቃዱ በጀትን ጨምሮ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም በማንኛውም ጊዜ ለመለወጥ ለፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ማመልከት ይችላል፡፡

፫/ በማንኛውም የሥራ ፕሮግራም ላይ ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ) ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም ለመተግበር ያላስቻሉትን ክስተቶች ወይም የባለፈቃዱን የቀድሞ ሥራ ፕሮግራም መሠረት በማድረግ ለውጡ ያስፈለገበትን የቴክኒክና የፋይናንስ ምክንያቶችን ለይቶ ማሳየት እና መሠረታዊ ለውጥ የሚደረግ ከሆነም አሳማኝ ምክንያቶችን ማቅረብ፣ እና

ለ) የታሰበውን የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያና በጀት መያዝና የሚከፈል ክፍያ ካለ መክፈል አለበት፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ ማመልከቻ በቀረበ በአሥር (፲) ቀን ውስጥ፡-

ሀ) ተሻሽሎ የቀረበው የሥራ ፕሮግራም አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ ተቀብሎ ያፀድቀዋል፣ ወይም

ለ) የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ለውሣኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

## ፳፩. ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ መብቶች

በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ተግባራትን ለማከናወን አስፈላጊ እስከሆኑና በፈቃዱ ላይ የተደረጉ ማናቸውም ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ የፈቃዱ ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስና ተፈጻሚነት ያላቸው ሌሎች ሕጎችን መሠረት በማድረግ ባለፈቃዱ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

፩/ በጀትን ጨምሮ ተቀባይነትን ባገኘ የሥራ ዕቅድ መሠረት በፈቃዱ የተዘረዘሩ የጂኦተርማል ሥራዎችንና እነዚህኑ ሥራዎች ለመሥራት አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም ተግባራት ለማከናወን ወደ ፈቃድ ክልል የመግባት፣

2/ The licensee may at any time apply to licensing authority to vary the approved work program, including budget.

3/ Any application for variation shall:

a) identify the events that prevent the licensee from carrying out the work program as approved, or identify the technical or financial basis for varying the work program based on prior work program of the licensee and provide justification for any substantive changes; and

b) be accompanied with the intended amendment of the work program and its budget, and discharge payment of fee, if any.

4/ After receiving the application for variation the licensing authority shall, within ten (10) days:

a) approve the variation work program, if convinced with the variation; or

b) shall notify the applicant in writing of the reasons for refusal, if it rejects the application for variation work program.

## 21. General Rights of Licensees

In addition to the rights provided for in the other provisions of this Proclamation, in so far as it may be necessary for the operations referred to in this Proclamation and subject to any restrictions specified in the license, the licensee shall, for the term of the license consistent with applicable laws, have the right to:

1/ enter the license area for the purposes of conducting activities specified in the geothermal operations license and to carry on any other necessary activity for the operation in accordance with approved work program including budget;

፪/ በሥራ ዕቅዱ መሠረት ወደ ፈቃድ ክልሉ ሠራተኞችንና ሥራዎቹን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ፋብሪካዎችን፣ ማሽነሪዎችንና መሣሪያዎችን የማስገባት፣

፫/ አግባብነት ያላቸው የውሃ ሀብት ሕጎችና የተፋሰስ ዕቅዶችን በማክበር፣ የተሻሉ የአሠራር ልምዶች፣ የጤናና ደህንነት ደንቦችና መመሪያዎች በማክበር ለሥራው አስፈላጊ የሆነ ውሃን በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ከሚገኝ የገፀ-ምድር፣ የከርሠ-ምድር ወይም አቋርጦ ከሚያልፍ ከማንኛውም የውሃ አካል የመጠቀም ወይም የውሃ ጉድጓድ የመቆፈር፣

፬/ የጂኦተርማል ሥራ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ከመሬት በላይ ወይም በመሬት ሥር የሚዘረጉ መሠረተ ልማቶችን የመዘርጋትና የመገንባት እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ፋብሪካዎችንና ማሽነሪዎችን መትከል ሕንፃዎችንና ሌሎች ግንባታዎችን የማካሄድ እና የማደስ፣

፭/ በፈቃድ ክልሉ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ለመዘርጋት በፍቃድ ክልሉ በሚገኙ የግንባታ ማዕድናት የመጠቀም፣

፮/ ማንኛውንም የጂኦተርማል ፈሳሽ የመያዝና የመጠቀም፣

፯/ አግባብነት ያላቸው የውሀ ሀብት ሕጎችን፣ የተፋሰስ ዕቅዶችንና ተያያዥነት ያላቸውን የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን በማክበር ጥቅም ላይ የዋለ ውሃን የማስወገድ፣

፰/ የደን ውጤቶችን ስለመቁረጥና በምትካቸው ችግኞችን ስለመትከል የወጡ አግባብ ያላቸው ሕጎችን በማክበር በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ለጂኦተርማል ሥራው ብቻ አስፈላጊ የሆኑ የደን ውጤቶችን የመቁረጥና የመጠቀም፣

፱/ ሌሎች ሰዎች እንዳይገለገሉባቸው መሰናክል በማይፈጥር ሁኔታ በነባር መንገዶች፣ ድልድዮችና የመሠረተ ልማት አውታሮች የመገልገል፣

፲/ በፈቃዱ መሠረት መሬቱን ጥቅም ላይ ለማዋልና ወደ ፈቃድ ክልሉ ለመግባት የሚያስፈልጉ መጋቢ መንገዶችን፣ ድልድዮችንና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን የአካባቢ ዕቅድንና የግንባታ ደረጃን ጠብቆ የመገንባትና የማደስ፣

2/ bring to the license area, in accordance with the work program, personnel and any plant, machinery and equipment;

3/ use water from any water body, situated on, under, or flowing through, such land or drill a well required for his activities, subject to the relevant Water Laws, relevant basin plans and upholding best practices and applicable health and safety regulations and directives;

4/ build and construct, any surface or underground infrastructure required for the purposes of geothermal resources operations and erect, construct and maintain such plant, machinery, buildings and other erections as may be necessary;

5/ use construction materials found within the license area as required for constructing essential physical infrastructure within the license area;

6/ reclaim and utilize any geothermal fluids;

7/ dispose used water consistent with Water Laws and relevant basin plans and related Environmental Laws;

8/ subject to the applicable laws regarding the cutting of timber and reforestation, cut and use timber that is strictly necessary for access to the licensed area and other geothermal resources operations;

9/ use the existing roads, bridges and communications infrastructure in a manner that does not impair the use of other persons;

10/ construct and maintain access roads, bridges and other means of communications consistent with environmental planning and construction standards to facilitate access to and use of the land pursuant to the license;

፲፩/ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችና መመሪያዎች በማክበር ለጂኦተርማል ሥራው አስፈላጊ የሆኑ ጉድጓዶችን የመቆፈርና የመገንባት፤

፲፪/ ለራሱና ለሠራተኞቹ መኖሪያ የሚያገለግሉ ጊዜያዊ ቤቶች ግንባታዎችን የማካሄድ፣ የመገንባትና የመጠገን እና እነዚህን ቤቶችና ግንባታዎች የመተው፤

፲፫/ ጂኦተርማል ፈቃድ ለመስጠት መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ በደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ላይ ከማመንጫ ተቋም የሚወጣ የጂኦተርማል ፍሳሽን ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ላልሆነ ተግባር በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ወይም በፈቃዱ ክልል አካባቢ የመጠቀም ወይም የመሸጥ፤

፲፬/ ባለፈቃዱ የውጭ ባለሀብት ሲሆን በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባለው የሂሣብ አሠራር መሠረት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሣብ የመያዝ::

፳፪. ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ ግዴታዎች

፩/ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተመለከቱ ሌሎች ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፈቃዱ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) የጂኦተርማል ሥራውን ተገቢ በሆኑ ሕጎች፣ ቴክኖሎጂና ለጂኦተርማል ሥራ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባገኘ የአሠራር ልምድ መሠረት የማካሄድ፤

ለ) የወኪሎቹን፣ የሠራተኞቹንና የሌሎች ሰዎችን ጤንነትና ደህንነት በሚያረጋግጥና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ወይም ብክላን መከላከል በሚያስችል ሁኔታ የጂኦተርማል ሥራውን የማከናወን፤

ሐ) ለጂኦተርማል ሥራው አስፈላጊ የሆነና በጂኦተርማል ኢንዱስትሪ ተቀባይነት ባገኘ የአሠራር ልምድ መሠረት ሁሉም ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና ያገኙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

11/ drill and construct wells necessary for geothermal operation in compliance with the relevant rules and directives;

12/ erect, construct and maintain temporary houses and buildings for his own or employees use or abandon such houses and buildings;

13/ utilize or sell for non-electrical purposes a geothermal fluids generating from facility within the license area or adjacent to it in a consistent manner with the licensing requirement of geothermal resources on Grade I geothermal resources;

14/ if the licensee is foreign investor, hold foreign currency bank account in accordance with accounting practices accepted in Ethiopia and directive issued by the National Bank of Ethiopia.

**22. General Obligations of Licensees**

1/ In addition to the obligations provided for under other relevant provisions of this Proclamation and other applicable laws, a licensee shall have the following obligations:

a) carry out geothermal operations in accordance with the appropriate laws, technology and geothermal operations consistent with international best practices generally accepted in the geothermal industry;

b) conduct geothermal operations to ensure the health and safety of licensee's agents, employees and other persons, and comply with the applicable laws pertaining to environmental protection;

c) ensure that all employees have received appropriate training and education necessary for geothermal operations consistent with best practices generally accepted in the geothermal industry;

መ) በፈቃዱ ክልልና አዋሳኝ በሆነ መሬት ላይ ሕጋዊ የይዞታ መብት ያላቸውን ሰዎች ላለማወክ ተገቢውን ጥንቃቄ የመውሰድ፣

ሠ) በፈቃድ ክልሉ ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ ለሚጠቀምባቸው እንደ መንገድ የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች ግንባታና ጥገናን በሚመለከት በተጠቃሚዎቹ የነፍስ ወከፍ የአገልግሎት መጠን ላይ ተመሥርቶ በሚደርስ ስምምነት መሠረት ገንዘብ የማዋጣት፣

ረ) በጂኦተርማል ሥራው ላይ እንቅፋት የማይፈጥርበት እስከሆነ ድረስ በዘረጋቸው የመንገዶችና የድልድዮች መሠረተ ልማ ቶች ሌሎች ሰዎች በነፃ እንዲጠቀሙ የመፍቀድ፣

ሰ) ድንገተኛ ሁኔታ ሲፈጠር፣ ለሚደርሰው ብልሽት ብቻ ካሣ በማስከፈል መንግሥት ወይም ሌሎች ሰዎች በመንገዱ፣ በሕንጻው፣ በመገናኛ መሣሪያዎቹ በመሳ ሰሉ መሠረተ ልማቶች በጊዜያዊነት እንዲ ገለገሉ የመፍቀድ፣

ሸ) ተፈላጊው ችሎታ ላላቸው ኢትዮጵያውያን የቅጥር ቅድሚያ የመስጠት፣

ቀ) በዋጋቸው ተወዳዳሪና በጥራታቸው ተመጣ ጣኝ ደረጃ ያላቸው እንደልብ ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ዕቃዎች ግዥና አገልግሎቶች ቅድሚያ የመስጠት፣

በ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚፈለግበትን ማናቸውንም ክፍያ በወቅቱ የመክፈል፣

ተ) ፈቃዱንና የሥራ ፕሮግራሙን የሚመለከቱ ማናቸውንም ሁኔታዎች የማክበር፣

ቸ) መዛግብቶችንና ሪከርዶችን ጨምሮ አግባ ብነት ያላቸውን ሰነዶች በሙሉ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በሌላ ሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች አካላት እንዲመረመሩ የማቅረብ፣

d) take proper precautions not to interfere with other legitimate occupants of the license area and adjacent land;

e) contribute financially in the construction and maintenance of infrastructure such as roads to be used jointly with other users within the license area as agreed upon the basis of proportional use of the infrastructure;

f) permit other persons to use its road and bridge infrastructure freely; provided, that such use does not impair its geothermal operations;

g) allow Government or other persons to use temporarily its roads, buildings and communications infrastructure in circumstances of emergency, subject only to the payment of compensation in the event of damage thereto;

h) give employment preference to the Ethiopian citizens, provided that such persons have the required qualifications;

i) give preference to the purchase and use of domestic goods and services, where they are readily available at a competitive price and are of a comparable quality;

j) discharge timely all payments required under this proclamation and regulation and directive issued hereunder;

k) comply with any terms of the license and provisions of work program provided in the license;

l) make available at reasonable time all relevant documents, including books and records, for inspection by the licensing authority or other duly authorized bodies under the relevant laws;

ኀ) የሰውን ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ድንገተኛ ሁኔታ ሲፈጠር መንግሥት ወደ ቦታው ገብቶ አስፈላጊውን እንዲፈጽም የመፍቀድ፣

ነ) በአካባቢና በኅብረተሰቡ ላይ የሚደርስ ተፅዕኖን የመቀነስና እንዲሁም ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ተቀባይነት ባገኘው የአካባቢና የኅብረተሰብ ላይ የሚደርስ ተፅዕኖ መቀነሻ ዕቅድ መሠረት እርምጃ የመውሰድ፣

ኘ) የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ሲያበቃ፣ ሲቋረጥ ወይም የፈቃድ ክልሉን በራሱ ፈቃድ ሲለቅ በፈቃድና በኪራይ ተይዞ በነበረው ቦታ የሚገኙ ጉድጓዶችና ሌሎች ሥራዎች በሰዎች ጤንነት፣ ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ እንዳያስከትሉ ተቀባ ይነት ባገኘው የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ግምገማ መሠረት ማጠር፣ ግንባታዎች ማንሳት፣ የቆፈራቸውን ጉድጓዶች በአግ ባቡ በመድፈን የመተው እና መከላከያ የማበጀት፣

አ) አግባብ ባለው አካል ዘንድ በንግድ መዝገብ ላይ የመመዝገብና ለፈቃዱ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ጽሕፈት ቤት የማቋቋም፣

ከ) በሚመለከተው ክልል ህግ መሠረት ለፈቃድ ክልሉና በኪራይ ለያዘው መሬት በየዓመቱ በቅድሚያ ክፍያ መክፈል፡፡

፪/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ኘ) መሠረት ያላነሳቸውን ግንባታዎች መንግሥት ያለምንም ክፍያ የራሱ ንብረት ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

## ፳፫. የፈቃድ ክልል ወሰን

፩/ የታወቀ የጂኦተርማል ክልል መጠንና ድንበር በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ይወሰናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከታወቀ የጂኦተርማል ክልል ውጭ የሚገኝ የጂኦተርማል ክልልን የሚመለከት ፈቃድ ለመስጠት በግሎባል ፖዚሽንንግ ሲስተም (በጂ.ፒ.ኤስ) ኮኦርድኔት የሚገለጹ

m) provide access to the Government to the facility so as to take necessary measures in an emergency situation affecting health and safety;

n) minimize impacts on the environment and communities and, where appropriate, provide mitigation for those impacts in accordance with the approved environmental and social plan;

o) fence, remove constructions and properly plug and abandon wells and otherwise safeguard in accordance with a duly approved environmental impact assessment any wells and such other works in the license or lease area so that the health, life and property of persons may not be endangered upon revocation, termination or surrender of the geothermal operations license or leased area;

p) get registered in the registry of trade with the competent body and shall maintain an office in Ethiopia during the entire term of any license;

q) to effect prior payment annually for the license and lease area in accordance with the law of the respective Regional State.

2/ The Government may takeover, free of charge, constructions not removed by a licensee pursuant to sub-article (1) (o) of this Article.

## 23. Boundaries of License Area

1/ The size and boundaries of known geothermal areas shall be determined by the licensing authority.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article and subject to the limitations of Article 7 of this Proclamation, for the purpose of licensing a geothermal resource area other than the known geothermal resource area, shall be limited by the perimeter of a geometric figure whose vertices

የማዕዘን ነጥብ ባሉት አንድ የጂኦሜትሪ ቅርጽ የወሰን መስመሮች ውስጥ የተወሰነ የቦታ መጠን የሚኖረው ሆኖ፡-

ሀ) ለቅኝት ፈቃድ ሲሆን ከሁለት ሺህ (፪ሺ) ስኩዌር ኪሎ ሜትር የማይበልጥ፤

ለ) ለምርመራ ፈቃድ ሲሆን ከሁለት መቶ (፪፻) ስኩዌር ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ሆኖ፣ አንድ ሰው እስከ ሁለት ፈቃድ ብቻ፤ ወይም

ሐ) ለጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ሲሆን ከሃምሳ (፶) ስኩዌር ኪሎ ሜትር የማይበልጥ የጂኦተ ርማል ሀብት ክልል ሊፈቀድ ይችላል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ዝርዝር አፈፃፀም አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

**፳፬. <u>የሌሎች አገልግሎቶች ፈቃድ ስለመደረብ</u>**

አግባብነት ያለው አካል ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጋር በመመካከርና ለአገሪቱ የሚያስ ገኘውን የኢኮኖሚ ጥቅምና በነባር ባለፈቃድ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ በተመለከተ አመልካቹ ያካሄደውን ጥናት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንዲሁም ነባሩን ባለፈቃድ በቅድሚያ በማሳወቅና በሥራዎቹና በአፈጻጸሙ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለማሣረፋቸውን አረጋግጦ በተመሳሳይ የፈቃድ ክልል ውስጥ ለሌሎች አገልግሎቶች ፈቃድ ደርቦ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፳፭. <u>ስለፈቃድ ቀዳሚነት</u>**

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ሀብቱን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ፈቃድ በመስጠት ሂደት በደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ መስጠት በደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ በሚሰጥ የጂኦተ ርማል ሥራ ፈቃድ ላይ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

are referred to in Global Positioning System Coordinates, and the following size of geothermal resources area may be authorize:

a) for a reconnaissance license it shall be not more than two thousand (2,000) square kilometers;

b) for an exploration license it shall be not more than two hundred (200) square kilometers; and a licensee shall not hold more than two licenses at time; or

c) for a geothermal well-field development and use license it shall be not more than fifty (50) square kilometers.

3/ the manner of detailed application of sub-articles (1) and (2) of this Article shall be determined in regulation issued pursuant to this Proclamation.

**24. <u>Superimposition of Licenses for Other Purposes</u>**

The competent body may, in consultation with the licensing authority and on the basis of the economic benefit to the country and assessment made by the subsequent applicant of the potential impacts on an existing licensee, grant licenses for other purposes within the same license area, upon notification to the holder of any existing license and as long as they do not materially affect the activities and performance of the existing license.

**25. <u>Precedence of Licenses</u>**

1/ Unless the licensing authority determines otherwise on the basis of an analysis of the economic benefits of the development of geothermal resources or other appropriate investment objectives, the granting of geothermal operations license on Grade I geothermal resources shall take precedence over granting geothermal operations license on Grade II geothermal resources.

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ሀብቱን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ፈቃድ በመስጠት ሂደት የምርመራ ፈቃድ በቅኝት ፈቃድ ላይ እና የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ በምርመራና በቅኝት ፈቃድ ላይ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

፫/ ፈቃድ በተሰጠበት ክልል በተደራቢ የተሰጠ ፈቃድ ቢኖር በክርክር ላይ ያለው የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ክልል በቀዳሚው ባለፈቃድ ይዞታ ሥር እንዳለ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

፳፮. <u>ፈቃድ ስለማስተላለፍ</u>

፩/ ከቅኝት ፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ የያዘ ባለፈቃድ በቅድሚያ የፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን የጽሑፍ ስምምነት በማግኘትና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የተመለከተ የፈቃድ ማስተላለፍ ክፍያ በመፈፀም ፈቃዱን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማንኛውንም ፈቃድ እንዲተላለፍ ከመፈቀዱ በፊት ፈቃድ እንዲተ ላለፍለት የሚፈልገው ሰው አስፈላጊው የገንዘብ አቅም፣ የቴክኒክ ችሎታና ልምድ ያለውና በማንኛውም ፈቃድ ሥር ያሉ ግዴታዎችንና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ በደንብና በመመሪያ የተዘረዘሩ ሌሎች መሥፈርቶችን የሚያሟላ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ ስምምነት ካልተገኘ በስተቀር ፈቃዱ የሚተላ ለፍባቸው ሰነዶች የሚከተሉትን የስምምነት ድንጋጌዎች ማካተት አለባቸው፡-

ሀ) ያለምንም ልዩነት ፈቃዱ የሚመለከተው ክልልና የፈቃዱ ሁኔታዎች በአጠቃላይ የሚተላለፉ መሆኑን፤ እና

ለ) ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው ተቀባይነት ባገኘው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለመፈ ፀም የተስማማ መሆኑን፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፱ (፩) እና (፪) ለተመለከተ ሰው ማንኛውም ዓይነት ፈቃድ አይተላለፍም፡፡

2/ Unless the licensing authority determines otherwise on the basis of analysis of economic benefits of the development of geothermal resources or other appropriate investment objectives, in the granting of licenses, an exploration license shall take precedence over a reconnaissance license, and a geothermal well-field development and use license shall take precedence over an exploration and reconnaissance license.

3/ If any license area is found to be superimposed upon that of another license, the area under dispute shall stay within the area of the first-issued license.

**26. <u>Transfer of License</u>**

1/ Any license, other than a reconnaissance license, may transfer his license to another person with the prior written consent of the licensing authority and upon payment of any transfer fees prescribed in the regulation issued hereunder.

2/ The licensing authority shall, prior to approving any transfer, ensure that the transferee has the necessary financial resources and technical capability and experience to fulfill the obligations under any license and meets such other criteria as may be set forth in the regulation and directive issued hereunder.

3/ The documents that transfer the licenses shall include the following provisions; unless prior written consent of the licensing authority is obtained:

a) the license area and the terms of the license are transferred in total, without exception; and

b) the transferee of the license agrees to adhere to any provisions of the approved work program.

4/ No license may be transferred to a person specified under Article 19 (1) and (2) of this Proclamation.

፭/ በሚተላለፍ ፈቃድ ሥር ያለ ማንኛውም መብት በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት አግኝቶ ካልተመዘገበ በቀር ፈቃዱ ተላልፏል ለተባለለት ሰው የሚያስገኘው ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

፳፯. <u>መብትን ስለመተው</u>

፩/ ባለፈቃዱ ፈቃዱን ወይም የፈቃድ ክልሉን የትኛውንም ክፍል በቅድሚያ ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን በጽሑፍ በማሳወቅ መተው ይችላል፡፡ ሆኖም መብቱን በራሱ ፍላጎት ከተወ በኋላም የለቀቀውን ቦታ ቀድሞ ወደነበረበት ሁኔታ የመመለስ ወይም በራሱ ተግባራት ምክንያት የተከሰቱ ብክለቶችን የማስወገድ ወይም ለዚህ ተግባር የሚውል ዋስትና ወይም ገንዘብ የማስያዝ የመሣሠሉት ግዴታዎች አሉበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የፈቃድ ወይም የኪራይ መብቱን የተወ ማንኛ ውም ሰው ፈቃዱ ወይም የኪራይ ውሉ ፀንቶ ለቆየበት ጊዜ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ከመፈፀም ነፃ አይሆንም፡፡

፳፰. <u>መረጃዎችን ስለመግለጽ</u>

፩/ የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት እንዳለው ወይም ሚስጥር መሆኑ በባለፈቃዱ ምልክት ተደርጎበት በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበ ማንኛውም መረጃ፣ ሪፖርት፣ ሰነድ ወይም ዳታ በባለፈቃዱ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ፈቃዱ ፀንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በሌላ የመንግሥት አካል ለሌላ ሦስተኛ ወገን መገለጽ የለበትም፡፡ ሆኖም ባለፈቃዱ በፈቃዱ ሥር የነበረ ክልልን ከተወ ወይም ፈቃዱ ከተሠረዘ በኋላ ማናቸውም የጂኦተርማል ሀብቱን የሚመለከቱ መረጃዎች ለሕዝብ ክፍት ይሆናሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ክልከላ፦

ሀ) በፍትሕ አካላት ዘንድ ለተያዘ ክርክር፣ ማጣራት ወይም ምርመራ ሲሆን፤

ለ) እንደዚህ ያሉ መረጃዎችን እንዲቀበል በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተፈቀደለት ከመንግሥት ጋር ውለታ ያለው አማካሪ ሲሆንና ይኸው አማካሪ በዚህ አንቀጽ

5/ Rights under any transfer of a license shall be ineffective as against any transferee of the license unless such transfer is approved and is registered by the licensing authority.

**27. <u>Surrender</u>**

1/ The holder of a license may surrender his license or any portion of the license area by giving notice to the licensing authority subject to obligations which shall continue following surrender, such as the obligation to restore the site or remediate pollution caused by licensee's operation, or to furnish guarantee or other financial instrument for that purpose.

2/ Any person who surrenders his license or lease right pursuant to sub-article (1) of this Article, shall not be released from the liability of performing the duties imposed upon him and due to be performed during the term of the license.

**28. <u>Disclosure of Information</u>**

1/ Any information, reports, documents, or data submitted pursuant to this Proclamation marked as proprietary or confidential by the licensee shall not be disclosed by the licensing authority or any other Government organ to a third party during the term of the license and any extensions thereof, except with the consent of the licensee; provided, however, that following surrender of license area or termination of license, all information related to the geothermal resources shall be public information.

2/ The prohibition of disclosure of information pursuant to sub-article (1) of this Article shall not apply when the information is sought:

a) for the purpose of legal proceedings, an inquiry or investigation conducted by an organ of justice administration;

b) to any person that is under contract as a consultant to the Government who is authorized by the licensing authority to receive such information; provided that such

መሠረት መንግሥት ሚስጥር ለመጠበቅ እንደገባው በተመሳሳይ ግዴታ ያለበት ሲሆን፤ ወይም

ሐ) ለጉዳዩ ከሚያስፈልገው በላይ ዝርዝር እስካል ሆነ ድረስ ለመንግሥት ወይም መንግሥትን በመወከል የልማት ሥራዎችን ስታትስቲክስ ለማጠናቀር ሲሆን፣ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

## ፳፱. ስለሪከርዶችና ሪፖርቶች

፩/ ማናቸውም ባለፈቃድ በፈቃዱ በግልጽ እንደሚያስፈልጉ ከተጠቀሱ ዝርዝር ሪከርዶችና ሪፖርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃ ዎች የያዙ ሰነዶችን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መያዝ እና እነዚህኑ ሪፖርቶች ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፦

ሀ) ስለጉድጓድና ከጉድጓድ ስለወጣ ኮር የተመዘገበ ዝርዝር ዳታ፣ ጉድጓዱም ስለሚሰጠው ምርት፣ ስለ ሪኢንጄክሽን ተግባራትና በጉድጓዶች መካከል ሊኖር የሚችል ተጽዕኖን ለመፈተሽ የተደረጉ ሙከራዎችን ጨምሮ የጂኦተርማል ሥራውንና የተገኙ ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን፤

ለ) የቅጥር፣ የፋይናንስ፣ የንግድና ሌሎች በፈቃድ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ በደንብና በመመሪያ የተመለከቱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን::

፪/ ባለፈቃዱ የፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን በጽሑፍ የተሰጠ ይሁንታን ሳያገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) የተመለከቱትን ማናቸውንም ከጉድጓድ ጋር የተያያዘ ወይም ከጉድጓድ የወጣ ኮር ወይም የኮሩን የተመዘገበ ዳታ ማስወገድ ወይም ማጥፋት አይችልም::

## ፴. ከጂኦተርማል ጋር የተያያዙ ናሙናዎችን ወደ ውጭ ስለመላክ

፩/ ባለፈቃዱ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ በጽሑፍ በተሰጠ ፈቃድ መሠረት የጂኦተርማል ፈሳሾችን፣ ብራይንና ሌሎች የጂኦሎጂካል ናሙናዎችን ወደ ውጭ ሀገር ለፍተሻ የመላክ መብት አለው::

consultant is bound by the same standard of non-disclosure as is the Government under this Article; or

c) for the preparation of statistics by or on behalf of the Government in respect of development operations; provided such disclosure is no more specific in detail than is necessary for the purpose of the statistics concerned.

## 29. Records and Reports

1/ In addition to specific records and reports that may be required in the license, any licensee shall make available within the territory of Ethiopia documents containing the following information and shall submit such reports to the licensing authority that include:

a) information pertaining to its geothermal operations and the results connected therewith, including, but not limited to, well and core-log data, production and re-injection activities and interference or tracer tests;

b) employment, financial, commercial and other relevant information as may be required in the license or as may be prescribed in regulation and directive issued hereunder.

2/ The licensee may not dispose of or destroy any document relating to well or core-log data specified in sub-article (1) (a) of this Article, without the prior written consent of the licensing authority.

## 30. Export of Geothermal Related Geological Samples

1/ The holder of a license shall have the right, with the prior written consent of the licensing authority, to export samples of fluids, brine and other geological related resources for laboratory testing.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጂኦተርማል ናሙናዎች መጠን፣ አያያዝ፣ ምርመራና ቁጥጥር አፈጻጸም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፴፩. <u>ስለቴክኖሎጂ ሽግግር</u>**

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ ከጂኦተርማል ሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በሚያደርግበት ጊዜ ስምምነቱን ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በማቅረብ ማስፈቀድና ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መቅረብ የሚገባቸው መረጃዎች እና መቅረብ የማይገባቸው የአዕምሯዊ ንብረት መረጃዎች በደንብና በመመሪያ ይወሰናሉ፡፡

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ ድንጋጌዎች ባለፈቃዱ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚሰጣቸው መሰል የቴክኖሎጂና የአዕምሮአዊ ንብረት ባለቤትነት መብቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፬/ ከባለፈቃዱ ጋር የሚደረጉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶች ከአገሪቱ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሕጎች ጋር የሚጣጣም መሆኑን ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**፴፪. <u>ፈቃድን ስለማገድ</u>**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወደ ፈቃድ ክልሉ በመግባት ቁጥጥር በማድረግ የባለፈቃዱ ተግባር በማኅበረሰቡ፣ በሠራተኞቹ ወይም በአካባቢ ላይ ከባድ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ሲያምንበትና ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ማገድ ብቸኛው መፍትሄ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃዱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማገድ ይችላል፡፡

፪/ የሕዝብን ጤና፣ ደህንነት ወይም አካባቢን ለመታደግ ፈጣን ምላሽ የሚያስፈልገው ድንገተኛ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃዱን ከማገዱ በፊት፡-

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the quantity, handling, control and inspection of geothermal samples shall be determined in regulation and directive issued hereunder.

**31. <u>Technology Transfer</u>**

1/ Any licensee who concludes a technology transfer agreement in connection with his geothermal operations shall submit same to the licensing authority for approval and registration.

2/ Information to be provided pursuant to sub-article (1) of this Article, as well as any excluded proprietary information, shall be determined in regulation and directive.

3/ The provisions of Article 28 of this Proclamation shall apply to the technology and proprietary ownership rights transferred by the licensee to the licensing authority.

4/ When considering entering into a technology transfer agreement with a licensee, the licensing authority shall ensure that the agreement is consistent with the technology transfer law of the country.

**32. <u>Suspension of Licenses</u>**

1/ Subject to sub-articles (2) and (3) of this Article, the licensing authority shall have the right to enter the license area and upon conducting supervision may suspend geothermal licenses in whole or in part when it believes that the activity of the licensee is or is likely to pose imminent danger to the local community, its employees, or the environment, provided that such suspension is the only remedy under the prevailing circumstances.

2/ Except in emergency circumstances in which immediate response is required to protect public health safety or the environment, before suspending the license, the licensing authority shall give notice in writing to the licensee:

ሀ) ፈቃዱን ለማገድ ምክንያት ናቸው የሚላቸውን ነገሮች፣ ባለፈቃዱ የፈፀማቸውን የዚህን አዋጅ፣ ሌሎች ሕጎችንና ደንቦችን ጥሰቶች ለማረም ሊወስዳቸው የሚገባቸውን በጊዜ የተገደቡ እርምጃዎች፤ እና

ለ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እገዳ ሊፈጸም አይገባም የሚላቸውን ማናቸውም ጉዳዮች በጽሑፍ የሚያቀርብበት ከሃያ (፳) ያልበለጠ በቂ የሥራ ቀን የያዘ፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የእገዳ ማስጠንቀቂያውን በማንሳት ባለፈቃዱ ወደነበረበት ሁኔታ ሥራዉን እንዲቀጥል የሚፈቅደው፡-

ሀ) ባለፈቃዱ ለፈቃዱ መታገድ ምክንያት ናቸው ተብለው የተዘረዘሩትን ነገሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ካረመ፣ በበቂ ሁኔታ ካሻሻለ፣ ካስወገደ ወይም እንዳይደገሙ ከተከላከለ፤ ወይም

ለ) እገዳ ሊፈፀም አይገባም በማለት ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶች ከተቀበለ፣ ይሆናል፡፡

## ፴፫. <u>ስለፈቃድ መሠረዝና መቋረጥ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ የሚሰረዘው፡-

ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃዱን ክልል በሙሉ ሲለቅ ወይም የፈቃድ መብቱን ሲተው፤

ለ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት ፈቃዱ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲሠረዝ፤

ሐ) የፈቃዱ ዘመን ከተፈፀመ በኋላ ሳይታደስ ሲቀር፤

መ) የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ሲሞት ወይም ባለፈቃዱ የሕግ ሰውነት መብት ያለው የንግድ ማህበር ከሆነ መፍረሱ ሲረጋገጥ ወይም የመክሰር ውሣኔ ሲሰጥበት፤ ይሆናል፡፡

a) setting out the grounds for suspension of the license, directing the licensee to take specific measures to remedy any violation of this Proclamation or other laws and regulations; determine a time period for the licensee to rectify, and any penalties for violations of applicable laws; and

b) specifying a reasonable date not exceeding twenty (20) working days, before which the licensee may, in writing, submit to the licensing authority's his objection against suspension.

3/ The licensing authority may lift the notice of suspension of a license and reinstate the licensee in good standing in circumstances in which:

a) the licensee complies with the requirement of the notice contemplated in sub-article (2) (a) of this Article by rectifying, removing, or mitigating the grounds for suspension, or by preventing the recurrence of such grounds within the time specified in the notice; or

b) the reasons submitted by the licensee in accordance with sub-article (2) (b) of this Article justify the lifting of the suspension.

## 33. <u>Termination and Revocation of License</u>

1/ A license issued pursuant to this Proclamation shall terminate if:

a) a licensee surrenders the whole license area;

b) a license is revoked by the licensing authority pursuant to the provisions of this Proclamation and regulation and directive issued hereunder;

c) a license expires without being renewed;

d) without prejudice to the rights of heirs, upon death of a licensee if he is a natural person and when liquidated or declared bankrupt if a licensee is a juridical person.

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ሊቋረጥ የሚችለው ባለፈቃዱ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የተመለከቱ የፋይናንስ ግዴታዎችን ካላከበረ፤

ለ) የጂኦተርማል ሥራዎችን በከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ አግባብ ባልሆነ መንገድ ካካሄደ፤

ሐ) የፈቃዱን መሠረታዊ ስምምነቶች ወይም ግዴታዎች ከጣሰ፤

መ) በሥራ ፕሮግራሙ መሠረት የጂኦተርማል ሥራዎችን የማያካሂድ ከሆነ፤

ሠ) የተፈቀደ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ተግባራዊ ያላደረገ ወይም የደህንነትና የጤና ደረጃዎችን ያላከበረ ከሆነ፤

ረ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት ማቅረብ ከሚገባው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ አቅርቦ ከተገኘ፤

ሰ) በማናቸውም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የተሟሉ፣ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታ የሚያሳዩ መዝገቦችንና ሪከርዶችን ካልያዘ ወይም በፈቃዱ መሠረት መቅረብ የሚገባቸውን ሪፖርቶች ወይም ሌሎች መዝገቦችን ካላቀረበ፤

ሸ) በአግባቡ ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደ ፈቃድ ክልሉ ወይም በኪራይ ወደተያዘው ክልል እንዳይገባ ወይም የጂኦተርማል ሥራዎች የሚካሄድ ባቸውን ቦታዎች ወይም ተቋማት ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፣ ሪከርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች ወይም ማቴሪያሎች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈፀመ፤

2/ A license issued pursuant to this Proclamation may be revoked if a licensee:

a) fails to comply with the financial obligations prescribed in this Proclamation and regulation and directive issued hereunder;

b) conducts geothermal operations in a grossly negligent or willfully improper manner;

c) breaches any material term or condition of its license;

d) is not conducting its geothermal operations in accordance with the approved work program;

e) is in breach of the approved environmental impact assessment, or safety and health standards;

f) has submitted false or fraudulent information in connection with any matter required to be submitted under this Proclamation and regulation and directive issued hereunder;

g) fails to maintain complete, accurate and current books and records or other documents or materials required by any regulation and directive issued hereunder or fails to submit reports or other documents as required by its license;

h) fails to grant a duly authorized official of the licensing authority access into the license area, or any area covered by a lease, or to any other site or premises of geothermal operations or to licensee's books, records, other documents or materials, or fails to carry out a lawful order or instruction of such official;

ቀ) በፈቃዱ ውስጥ በተቀመጠው መሠረት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ ያለበትን አስፈላጊ መሠረታዊ መረጃ ያላቀረበ ከሆነ፡፡

፫/ በፈቃዱ ወይም በሌላ ስምምነት፣ በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በቀር በደረጃ I ወይም በደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ የሚሰጥ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ሲቋረጥ ለጂኦተርማል ሥራዎች ጥቅም ላይ ውለው የእርጅና ቅናሻቸው ሙሉ በሙሉ ያልተጠናቀቁ ጉድጓዶችን ሳይጨምር የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በባለፈቃዱ የሂሣብ መዝገብ ላይ በሚታየው ዋጋቸው መንግሥት ሊገዛቸው ይችላል፡፡

፬/ መንግሥት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱ ንብረቶችን ሊያነሳቸው ካልቻለ፣ ባለፈቃዱ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ንብረቶቹን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፣ ንብረቱ ሊተላለፍ የማይችል ከሆነ ስለአካባቢ ጥበቃ በገባቸው ግዴታዎች መሠረት ያስወግዳቸዋል፡፡

**፴፬. <u>የጂኦተርማል የማማከር አገልግሎት ወይም የቴክኒክ ነክ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>**

፩/ ማንኛውም በጂኦተርማል የማማከር አገልግሎት ላይ መሠማራት የሚፈልግና ከጂኦተርማል ጋር የተያያዘ ሙያ ያለው ግለሰብ በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ መሠረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም በጂኦተርማል የማማከር አገልግሎት ወይም ቴክኒክ ነክ ሥራ ላይ መሠማራት የሚፈልግ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማህበር በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል፡፡

i) fails to submit to the licensing authority as required by the license, any material information.

3/ Upon termination of a geothermal operations license granted on Grade I or Grade II geothermal resources, the Government may, unless a license or another agreement specifies otherwise, buy all of the immovable and movable property, excluding wells, used in the geothermal operations at a price equal to the then unamortized value of such assets, as shown in the financial book of accounts of the licensee.

4/ If the Government does not acquire the properties specified under sub-article (3) of this Article in one year or in such other time set forth in regulation issued hereunder, the licensee shall be free to transfer such assets to another person in accordance with the applicable laws, or shall remove them as required by its environmental obligations if cannot be transferrable.

**34. <u>Certificate of Professional Competency for Geothermal Consultancy Service and Technical Works</u>**

1/ Any individual with geothermal related profession who wishes to engage in geothermal consultancy services may apply for a certificate of professional competency to the licensing authority in accordance with this Proclamation and Regulation issued hereunder.

2/ Any juridical person wishes to engage in geothermal technical works or geothermal consultancy services may apply for a certificate of competency to the licensing authority in accordance with this Proclamation and Regulation issued hereunder.

## ክፍል አምስት
## ስለ አስተዳደር፣ ስለካሣ ክፍያ፣ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ስለመሆን፣ ስለፈቃድ ክፍያ እና ስለአካባቢ ደህንነት

፴፭. ስለ ቁጥጥር

፩/ ማንኛውም ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ተገቢ በሆነ የሥራ ሰዓት ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የጸና መታወቂያ ካርድ በማሳየት ወደማንኛውም የፈቃድ ክልል በመግባት፦

ሀ) የፈቃድ ክልሉንና በፈቃድ ክልሉ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለን ማናቸውንም እንቅስቃሴ ወይም ሂደት ለመቆጣጠር፣

ለ) ማንኛውንም ሪከርድ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ ለመመርመርና የሰነዱን ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅ ለመውሰድ፣

ሐ) ማናቸውንም ናሙና ለመውሰድና ለመፈተሽ፣ ለመመርመር፣ ለመተንተንና በዓይነት በዓይነቱ ለመለየት፣ ይችላል፡፡

፪/ ባለፈቃዱ ሥልጣን ለተሰጠው ተቆጣጣሪ ድጋፍ የሚሰጥ አግባብ ያለው ሠራተኛ መመደብና በፈቃዱ ክልል ውስጥ ባለ ጊዜ ሁሉ ደህንነቱን የማረጋገጥና በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች ሠራተኞች የታደለውን የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያ መስጠት አለበት፡፡

፫/ ሥልጣን የተሰጠው ተቆጣጣሪ በማስረጃዎችና በአካባቢ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መጣሳቸውን፣ እየተጣሱ ወይም ሊጣሱ መሆኑን ካመነ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጽሑፍ በሚሰጠው ይሁንታ መሠረት አስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ ክስ ለመመሥረት አስፈላጊ የሆኑ መዝገቦችን፣ ሪከርዶችን፣ መግለጫዎችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ደረሰኝ በመስጠት ለመያዝና በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጥበቃ ሥር ለማቆየት ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) መሠረት ናሙና ሲወሰድ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ማንኛውም ሰነድ ሲያዝና በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጥበቃ ሥር እንዲቆይ ሲደረግ፦

## PART FIVE
## ADMINISTRATION, COMPENSATION, EXEMPTION FROM CUSTOMS DUTIES, LICENSE FEES AND ENVIRONMENTAL SAFETY

35. **Inspections**

1/ Any authorized inspector of the licensing authority during appropriate working hours, upon showing valid identity card issued by the Authority, may enter any license area:

a) inspect the license area and any activity or process carried out in the license area;

b) inspect any record, statement or other document and make copies or extracts thereof;

c) take samples of any material for the purpose of testing, examining, analyzing and classifying such samples.

2/ The licensee shall provide the authorized inspector an appropriate employee to assist him and shall take reasonable measures to ensure that the inspector's safety while in the license area, including provision of safety equipment generally distributed to the employees working in the license area.

3/ In the event that the authorized inspector has the logical belief, supported by facts and circumstances, that a violation of the terms of this Proclamation has been, is being, or will be committed; the inspector may with the written approval of the licensing authority, by giving receipt, may seize any book, record, statement or other document deemed relevant to administrative or judicial proceedings and keep same in the custody of the licensing authority.

4/ When any material is taken pursuant to sub-article (1) (c) of this Article or when any document is seized under sub-article (3) of this Article, and is in the custody of the licensing authority:

ሀ) በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር የነበረ ሰነድ የተያዘበት ሰው እነዚሁ ሰነዶች ከመወሰዳቸው በፊት ተቆጣጣሪው እየተከታተለው የሰነዱን ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅዎች እንዲወሰድ ማድረግ ይቻላል፤ ወይም

ለ) ከተያዘው የትኛውም ነገር ጋር በተያያዘ ክስ ካልተመሠረተ ወይም በማናቸውም ክርክር ወቅት እንደማስረጃ ሊያገለግል መቻሉ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለተያዘበት ሰው ወዲያውኑ ይመለሳል::

a) the person from whose possession or control any document is taken shall be allowed, under the supervision of the inspector, to make copies, extracts, or descriptions thereof prior to their removal; or

b) if no legal proceedings are instituted in connection with any of the items seized, or if it appears that seized materials are not required as evidence or upon court order, that item shall be returned immediately to the person from whom it was seized.

፴፮. <u>የሠራተኞች ጥበቃ</u>

ማንኛውም ባለፈቃድ የፈቃድ ግዴታዎቹን ወይም ይህን አዋጅ፣ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጣ ደንብና መመሪያን አለማክበሩን በሥሩ የሚገኝ ሠራተኛ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም ለሌላ ለማንኛውም ሥልጣን ለተሰጠው ሰው በማሳወቁ ምክንያት በሠራተኛው የሥራ ሁኔታ ላይ ጎጅ ተጽዕኖ የሚያደርስ እርምጃ ሊወሰድ አይችልም::

36. **<u>Protection of Employees</u>**

The holder of any license may not subject any of its employees to any occupational detriment on account of any such employees disclosing information to the licensing authority or any other authorized person regarding the failure by such holder to comply with its license or with any provision of this Proclamation and regulation, directive issued hereunder.

፴፯. <u>ስለ ካሣ</u>

ማንኛውም የጂኦተርማል ሥራ ለማከናወን መሬትን ማስለቀቅ የሚጠይቅ ባለፈቃድ ለሚለቀቀው የመሬትና ንብረት ባለይዞታ ለሕዝብ ጥቅም መሬት የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታዎች ለመወሰን በወጣ አዋጅ መሠረት ካሣ መክፈል አለበት::

37. **<u>Compensation</u>**

Where any geothermal operation requires the expropriation of land, the licensee shall pay compensation to the expropriated land use and property in accordance with the payment of compensation for expropriation of property for public interest Proclamation.

፴፰. <u>የአካባቢና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ</u>

፩/ የጂኦተርማል ሥራ ለማከናወን ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው፣ ከቅኝት ፈቃድ በስተቀር የአካባቢና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ አግባብ ላለው አካል አቅርቦ ማፀደቅ አለበት::

፪/ ከቅኝት ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ባለፈቃድ የፈቃድ ክልሉን ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ከነበረበት ሁኔታ በተሻለ ወይም በነበረበት ሁኔታ ለመመለስ የሚውል ፈንድ ይመድባል::

38. **<u>Environmental and Social Impact Assessment</u>**

1/ Any person lodging application to obtain geothermal operations license, except for a reconnaissance license, shall submit an environmental and social impact assessment document to competent body and get approval.

2/ Any licensee shall, except the holder of reconnaissance license, allocate funds to cover the cost of restoration of the license area to conditions as good as or better than conditions prior to the license period.

**፴፱. <u>ተፈጥሮአዊና ባሕላዊ ሀብቶችን ስለመንከባከብና መጠበቅ</u>**

ባለፈቃዱ የጂኦተርማል ሥራውን በጂኦተርማል ወይም በሌላ የኃይል ወይም የማዕድን ሀብት ላይ አስፈላጊ ያልሆነ ብክነት ወይም ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ፤ በገፀ–ምድርና በከርሡ–ምድር ውሃ ሀብቶች ጥራት ላይ እንዲሁም በአየርና በሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የዱር እንስሳትን፣ አፈርና እጽዋትን ጨምሮ በባህላዊ ሀብቶችና በአርኪዎሎጂ ቅርሶች፣ የተፈጥሮ መስህቦችና ለመዝናኛ የሚውሉ ሀብቶች ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ ማካሄድ አለበት፡፡

**፵. <u>ስለሰዎችና ንብረት ደህንነት</u>**

፩/ ባለፈቃዱ የጂኦተርማል ሥራው የሰውን ጤናና ደህንነት በጠበቀና በንብረት ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ ማካሄድ አለበት፡፡

፪/ ባለፈቃዱ በሥራው ምክንያት ሆን ተብሎም ይሁን በቸልተኝነት በሌላ በማንኛውም ሰው ወይም ንብረት ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጥፋት፣ ጉዳት ወይም አደጋ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፵፩. <u>ስለማኅበረሰብ ልማት ፈንድ</u>**

የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት ያመለከተ ሰው ባመለከተበት የፈቃድ ክልል ውስጥ ወይም አካባቢ ከሚኖሩ ነዋሪዎች ጋር በመመካከር በጽሑፍ የተዘጋጀ የኅብረተሰብ ልማት ዕቅድ ማካተት አለበት፡፡ ዕቅዱ የነዋሪዎቹን ማኅበራዊ ተቋማት ለማሻሻል የሚመደበውን ፈንድ ጨምሮ የዕቅዱን ማስፈፀሚያ መርሃግብር መያዝ አለበት፡፡

**፵፪. <u>ስለጂኦተርማል ሥራዎች መዘጋት የምስክር ወረቀት</u>**

ባለፈቃዱ ፈቃዱ ሲሠረዝ፣ ሲቋረጥ ወይም ሥራውን ሲተው ይህን አዋጅ ተከትሎ በወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የጂኦተርማል ሥራዎቹን በአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ዕቅድ በሚያዘው መሠረት መዝጋቱን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

**፵፫. <u>የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መፍትሔ የመስጠት ሥልጣን</u>**

፩/ ባለፈቃዱ የሞተ እንደሆነ ወይም ሊገኝ ካልቻለ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ማህበር ሲሆን ህልውናው ካከተመ ወይም በኪሣራ ከተዘጋ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የአካባቢ ተጽዕኖን ለመከላከልና የኅብረተሰቡን ጤና፣ ደህንነትና ማኅበራዊ ተቋማት ለመጠበቅ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

**39. <u>Preservation and Protection of Natural and Cultural Resources</u>**

Geothermal operations shall be carried out in such a manner as to prevent unnecessary waste of or damage to geothermal or other energy and mineral resources; to protect and enhance the quality of surface and ground waters, air and other natural resources, including wildlife, soil and vegetation; and preserve cultural resources, including archeological, scenic and recreational resources.

**40. <u>Safety of Persons and Property</u>**

1/ Geothermal operations shall be carried out in a manner that protects human health and safety and prevents damage to property.

2/ A licensee shall be liable for any loss, damage or injury to any person or property resulting from its operations, whether intentionally or as a result of negligence.

**41. <u>Fund for Community Development</u>**

Any person lodged application for geothermal well-field development and use license shall include a written community development plan, developed by the applicant in consultation with the communities existing in or adjacent to the license area; and such plan shall include an implementation plan including allocation of funding to support community welfare.

**42. <u>Geothermal Operation Closure Certificate</u>**

A licensee upon revocation, termination or surrender of license shall apply to the licensing authority to obtain a geothermal operation closure certificate, after proving that the closure has been undertaken in accordance with the environmental and social impact plans provided for in regulation and directive issued hereunder.

**43. <u>Remedial Powers of the Licensing Authority</u>**

1/ In the event the holder of a license is deceased, cannot be traced, or in case a juridical person ceases to exist or has been liquidated, the licensing authority may take the necessary measures to address environmental impacts and ensure protection of the public health, safety and welfare.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልገው ገንዘብ ባለፈቃዱ ለዚህ ተግባር ብሎ ካስቀመጠው የአካባቢ ፈንድ ወጪ ይሆናል፡፡

**፵፬. ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለመሆን**

፩/ ማንኛውም የጂኦተርማል ሥራ ባለፈቃድ ለሥራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው አላቂ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ፡፡

፪/ ማናቸውም በዚህ አንቀጽ መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ የገባ ዕቃ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ በጽሑፍ ሳይፈቅድና ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በማንኛውም ሁኔታ በአገር ውስጥ ለሌላ ሰው አይተላለፍም፤ ሆኖም ዕቃው ተመልሶ ከሀገር የሚወጣ ከሆነ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናል፡፡

**፵፭. ስለፈቃድ ክፍያ**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ የፈቃድ ማውጫ ክፍያ ይፈፀማል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ ፈቃድ በየዓመቱ የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ ሲፈጸም የሚታደስ ይሆናል፡፡

፫/ የፈቃድ ማውጫ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ የአከፋፈል ሁኔታና የገንዘቡ መጠን ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፵፮. አለመግባባቶችን ስለመፍታት**

፩/ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንና በባለፈቃድ መካከል ከውል በመነጨ ወይም ከፈቃድ ጋር በተያያዘ የሚፈጠር ማንኛውም ክርክር፣ አለመግባባት ወይም የይገባኛል ጥያቄ በተቻለ መጠን በጋራ ውይይት ይፈታል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንና ባለፈቃዱ በሚያደርጉት ውይይት አለመግባባቱ በዘጠና (፺) ቀናት ውስጥ ሊፈታ ካልቻለ በግልግል ዳኝነት ሥርዓት ታይቶ ውሣኔ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

2/ The measures contemplated under sub-article (1) of this Article shall be funded from the proceeds of environmental funds allocated by the licensee.

**44. Exemption from Customs Duties and Taxes**

1/ Any holder of a geothermal license shall be exempted from customs duties and taxes including value added tax for importing into Ethiopia any consumables, equipment, machinery and vehicles required for his operations in accordance with the approved work program.

2/ Any item imported into Ethiopia free of customs duties and taxes pursuant to the provisions of this Article shall not be transferred in Ethiopia to any person in any manner without having obtained a written permission from the license authority and paid the required duties and taxes; provided, however, that such items may be re-exported free of customs duties and taxes.

**45. License Fees**

1/ License fee shall be paid for issuance of license pursuant to this Proclamation.

2/ A license issued pursuant to sub-article (1) of this Article shall be renewed annually upon payment of license renewal fees.

3/ The amount and manner of payment of license issuance and renewal fees shall be determined by regulation to be issued hereunder.

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**46. Settlement of Disputes**

1/ Any dispute, controversy or claim between the licensing authority and a licensee arising out of, or relating to any agreement or license shall, to the extent possible, be resolved through negotiation.

2/ In the event that agreement between the licensing authority and a licensee cannot be reached through negotiations within ninety (90) days, the case shall be settled through arbitration procedure.

፫/ በግልግል ዳኝነት በሚሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ውሣኔው በተሰጠ በሠላሳ (፴) ቀናት ውስጥ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

**፵፯. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያ ዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፵፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ፪ (እንደተሻሻለ) መሠረት ከጂኦተርማል ሥራ ጋር በተያያዘ የተሰጠ ፈቃድና የተደረገ ስምምነት ፀንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን ተፈፃሚነቱ ይቀጥላል፡፡

፪/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ፪ (እንደተ ሻሻለ) መሠረት ከጂኦተርማል ሥራ ጋር በተያያዘ ፈቃድና ስምምነት ያለው ባለፈቃድ በማንኛውም ጊዜ በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የተመለከተ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፡፡

፫/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈጠረ ለክስ መነሻ የሚሆን ጉዳይ ወይም የተጀመረ ክርክር ወይም የአፈፃፀም ሂደት ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ፀንተው በነበሩ ሕጎች መሠረት ፍፃሜ ያገኛል፡፡

**፵፱. ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች**

፩/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፪/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፰ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ፪ (እንደተሻሻለ) ጂኦተርማል ሀብትን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

3/ Any party aggrieved by the arbitral award may lodge appeal within thirty (30) days to the High Court.

**47. Power to Issue Regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The licensing authority may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

**48. Transitory Provisions**

1/ Any license issued and agreement concluded in relation to geothermal operations pursuant to Mining Operations Proclamation No. 678/2010 (as amended) prior to the coming into force of this Proclamation shall continue in force for the remaining period of its validity.

2/ A holder of a license issued or agreement concluded in relation to geothermal operations pursuant to Mining Operations Proclamation No. 678/2010 (as amended) prior to the coming into force of this Proclamation may apply at any time for a license in accordance with this Proclamation, and regulation and directive issued hereunder.

3/ Any cause of action materialized or legal proceeding pending before the coming into force of this Proclamation shall be dealt with in accordance with the laws in force prior to the effective date of this Proclamation.

**49. Inapplicable Laws**

1/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

2/ Without prejudice to the provisions of Article 48 of this Proclamation, the Mining Operations Proclamation No. 678/2010 (as amended) shall not be applicable with regard to geothermal resources.

፶. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መስከረም ፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም.

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**50. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this16th day of September, 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERA DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**